የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ዓለም አቀፍ የምእመናን ማሕበር
WORLD ASSOCIATION OF PARISHIONERS OF THE ETHIOPIAN ORTHODOX TEWAHEDO CHURCH
4002 Blacksmith Drive, Garland, TX 75044, U.S.A. WWW.eotcipc.org
(813)312 1502; e-mailmiimenan@yahoo.com

ታሕሣሥ 4 ቀን 2003 ዓ/ም

በስመ አብ ወወልድ፤ ወመንፈስ ቅዱስ፤ አሐዱ አምላክ። አሜን።

መግለጪያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን ምእመናን ዓለም-አቀፍ ማሕበር ሁለተኛ ጉባኤ

"ግብዝነት የሌለበት እውነተኛ ፍቅር ይኑራችሁ፤ ክፉውን ነገር ጥሉ መልካሙን ነገር ተከተሉ፤ በክርስቶስ ውንድማማቾች እንደ መሆናችሁ መጠን እርስ በርሳችሁ ከልብ ተዋደዱ።" ሮሜ 12/9-10

በመጀመሪያ፤ ይህንን መግለጪያ ለሚመለከቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን አባቶችና ምእመናን ሁሉ ማሕበራችን የአክብሮት፤ መንፈሳዊ ሰላምታውን በትሕትና ያቀርባል።

በመቀጠልም፤ **ሁለተኛው ዓለም-አቀፍ የቤተ ክርስቲያናችን ምእመናን ጉባኤ፤ መስከረም 19 እና 20፤ 2004 ዓ/ም፤** ርእሰ አድባራት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን፤ ዋሺንግተን ዲ.ሲ. ሰሜን አሜሪካ የሚከናወን መሆኑንና ስብሰባው የሚያተኵርባቸው አርእስቶችም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መሆናቸውን እናስታውቃለን፤

1. ማሕበሩን ለማጠናከር፤ (ስለ መተዳደሪያ ደንቡ፤ ስለ አወቃቀሩ፤ ስለ መገናኛ ብዙኃን አጠቃቀም፤ አባላትን ስለ ማብዛት፤ ስለ ችሎታ ማዳበር፤ ወዘተ)፤
2. በአመራር ላይ ያሉ የልዩ ልዩ ደብሮች ምእመናን ተገናኝተው ስላጋጠሙዋቸው ችግሮችና መፍትሔዎች መወያየት፤
3. ወጣቶች በቤተክርስቲያናችን ትምሕርት እንዲሠለጥኑ ስለሚያስፈልጉት ጉዳዮች፤(ይህ አርእስት ት/ቤት የማጠናከርንም/የማቋቋቋምንም ሐሳብ ይጨምራል።)
4. የቤተ ክርስቲያናችን ትምሕርትና እምነት በዓለም-አቀፍ ደረጃ እንዲስፋፋ፤ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች (ለምሳሌ፤ በእንግሊዝኛ) ስለ መጠቀም፤
5. የአብነት ት/ቤቶችን ስለ መርዳት፤
6. ኢየሩሳሌም የሚገኘው ታሪካዊ ገዳማችን ተገቢው ጥገና እንዲከናወንለት ስለ ማድረግ።
7. በኢትዮጵያ ስለ ተከሰተው የቤተ ክርስቲያናችን ሁኔታ፤(በዚህ አርእስት ውስጥ፤ ስለ ቤተ ክርስቲያናችን አጠቃላይ ሁኔታ፤ ማለትም ስለ አስተዳደሩ፤ ስለ ደብሮችና ገዳማት ችግር፤ ስለ አክራሪ እስላሞች ሁኔታ፤ ስለ ስብከት ማጠናከር፤ ወዘተ.ጉዳዮች ይካተታሉ።)

## መንፈሳዊ ጥሪ፤

ከላይ በተጠቀሱት አርእስቶች ጥናታዊ ጽሑፍ ለማቅረብ ፈቃደኛ የሆናችሁ ካሕናትና ምእመናን እንዲሁም ተገቢ የሆኑ ምሑራንን ለመጠቆም የምትፈልጉ ሁሉ እስከ ሚያዚያ 30 ቀን 2003 ዓ/ም ድረስ ለጉባኤው ጽ/ቤት እንድታስታውቁ ይህንን ጥሪ እያስተላለፍን፤ በአጠቃላይ ጉባኤው የተሳካ ይሆን ዘንድ ካሕናትና ምእመናን በጸሎት፤ በሓሳብና በገንዘብ ድጋፍ እንድታደርጉ፤በጉባኤው ለመሳተፍ እንድትችሉም አስቀድማችሁ ጊዜያችሁን እንድታመቻቹ መንፈሳዊ ጥሪያችንን በእግዚአብሔር ስም በትሕትና እናስተላልፋለን።

ለሚደረግልን ድጋፍና መተባበር፤ ማሕበሩ በቅድሚያ ምሥጋናውን ይገልጻል።
ቸሩ የኢትዮጵያ አምላክ ጥረታችንን ባርኮ ለቁም-ነገር ያብቃን።

**የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ዓለም አቀፍ ማሕበር ግብረ-ኃይል።**